# ከህግ ፍርሃት በስተጀርባ

ከሰሞኑ የፀረ አሸባሪነት ረቂቅ ህግ ወጣ ሲባል ስሰማ እስከ አሁን ለምን ቆየ የሚል ጥያቄ ሳወጣና ሳወርድ ነበር። ሆኖም ጭራሽ ህጉ ያስፈራናል የሚሉ ወገኖች ብቅ ማለታቸው ደግሞ ዝብርቅርቅ ያለ ስሜት ፈጠረብኝ። እናም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ከሆነው ጓደኛዬ አፈላልጌ ረቂቅ ህጉን ለማንበብ ሞከርኩኝ። ህጉ ያስፈራናል ያሉትንና በግል ጋዜጦች የፊት ገፅ የፍርሃት ገፅታ ተላብሰው የወጡትን የተለያዩ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ፎቶና አስተያየቶች በማገናዘብ ለኔ የገባኝን ያህል በህግ ማዕቀፉ ላይ ያለኝን አስተያየት እንዲህ ፃፍኩት።

<u>**የሽብር ድርጊቶች ዳራ በኢትዮጵያ**</u>

ያኔ አክራሪዎች በአዲስ አበባ ከተማ በግብፁ ፕሬዘዳንት ላይ የግድያ ሙከራ ሲያደርጉ ሁለት ነገሮችን አስተዋልን። እንዴት በግልፅ ለመጡብን ግዙፍ ወራሪ መንግስታት ያልተበገረ ህዝብና አገር በጥቂት አክራሪዎች ድንበሩ ተጥሶ ለዛውም መሃል አገር አዲስ አበባ ድረስ መጥተው እንግዳችንን ተተናኮሉብን የሚለው የቆየው የአይበገሬነት ወኔያችን መነጋገሪያ ሆነ። በሌላ ወገን በእለቱ አክራሪዎቹ ሳይሳካላቸው እንዲቀር ያደረጉ ያልሞ ተኳሾቻችን ብቃት አኮራን።

ይህ እንደ አንድ ክስተት አለፈ ስንል በህዝብ ተቋማት፣ በሆቴሎችና በባቡር መጓጓዣ ሃዲድ ጥቃት ሲሳተፉ የነበሩ የተባሉ ሰዎች በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብለው ሲናዘዙ አስተዋልን። ድርጊቶቹም የተፈፀሙት ከውስጣችን የበቀሉትና ልዩ ልዩ የህዝብ ዓላማ ማንገባቸውን ሲነግሩን የነበሩ ኦነግ ፣ ኦብነግና የእስልምና ግንባር ለኦሮሚያ ነፃነት የተባሉ ድርጅቶች ተልእኮን ለመፈፀም እንደነበር ነገሩን።

ከነዚህ ድርጅቶች ጋር የነበረው ተያያዥነት በወቅቱ ይፋ ባይደረግም የአሜሪካው የሰላም ተቋም በኢትዮ - ሶማሌ ክልል ሽብርተኝነትን የሚያራምድ አል-ኢትሃድ አል-ኢስላሚያ የተሰኘ ድርጅት ስር እየሰደደ መሄዱን ይፋ አደረገ። ይህን ተከትሎም በ1996 እና በ1997 በአዲስ አበባ የቦምብ ጥቃቶች ተፈፀሙ። እነዚህን የብዙ ንፁሃን ዜጎች ህይወት የቀጠፈና ዜጎች መዝናኛዎች ውስጥ ሲሆኑ ሁልጊዜ በስጋት ውስጥ ታጥረው በተዘበራረቀ መንፈስ እንዲያሳልፉ ያስገደዱ ድርጊቶችን እንደ መልካም ፍፃሜ እኛ ነን ያደረግነው የሚሉ ድርጅቶች ብቅ አሉ። አል-ኢትሃድ ይህን የሚነግርበት የመገናኛ ብዙሃንም አላጣ። አፍታ ሳይቆይ አፈነዳኋቹህ፣ ገደልኳቹህ እናም እቀጥልበታለሁ ብሎ የወደፊት የሰላምና ልማት እጣ ፈንታችን በእጁ መሆኑን ነገረንና አረፈው።ለዚህም ነው  ኢትዮጵያ ስለሽብርተኝነት ጠንቅቃ ታውቃለች ብሎ በይፋ የአሜሪካው የሰላም ተቋም በወቅቱ ያወጀውና ዓለም አቀፍ የፀረ አሸባሪነት ጥምረትና ጥረት የተጀመረው።

የተቋሙ ጥናት እንደሚያመለክተው በሱማሊያ ከሃገር በቀሉ አል- ኢትሃድ በስተቀር ይህ ነው የሚባል በውጭ ዜጎች የተመሰረተ የሽብር ቡድን ያልነበረ ቢሆንም ቅርንጫፉን ለማስፋፋት ደግሞ ጊዜ አልፈጀበትም ይለናል። አል-ኢትሃድ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ይወስዳቸው የነበሩ የሽብር ጥቃቶች ቅርንጫፍ የሆነው ኦብነግ በ1996 እና 1997 በአዲስ አበባ  የህዝብ መገልገያ ተቋሚትና በንፁሃን ዜጎች ላይ የወሰደው አስከፊ

የሽብር ጥቃት በኛ ወገን ልንጠቅሰው የምንችል መሆኑን ልብ ይሏል። ከዚህ ባለፈ በኬኒያ ለሚፈፀመው የሽብር ተግባር አልቃይዳ ሶማሊያን ለመሸጋገሪያነት ተጠቅሞባታል።

## ከስብስብ ወደ ክፍልፋይ አል-ኢትሃድ

ኢህአዴግ መላ ሀገሪቱን በሚቆጣጠርበት እ.ኤ.አ 1992 መጨረሻዎቹ አካባቢ በጎረቤት ሶማልያም የተፈጠረ ክስተት ነበረ። የአል-ኢትሃድ ኃይል በጥንት ላንድ በአብዱላሂ የሱፍ ኃይል ትልቅ ሽንፈት እንደደረሰበት ተዘግቦ ነበር።ይህን ተከትሎም አል ኢትሃድ ወደ ኢትዮ-ሶማሌ አካባቢ ማምራቱም ጭምር። በወቅቱ ወደ ኢትዮ-ሶማሌ ክልል እንዲገባ የረዱትን ሁለት ምክንያቶች በዋናነት ይጠቅሳሉ ዘገባዎች። ምክንያቶቹም ኢህአዴግ አገሪቱን በተቆጣጠረበት ወቅት የኢትዮ-ሶማሌን ክልል ሙሉ በሙሉ ያለመቆጣጠሩንና ሶማሊያ በእርስ በርስ ጦርነት በታመሰችበት ወቅት አል-ኢትሃድ ወደ ኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ከጎረፉ የሶማሌ ስደተኞች ጋር በመቀላቀል እንዲገባ ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸው ነበሩ።

በመሆኑም በወቅቱ አል-ኢትሃድ ከኢትዮ-ሶማሌ አካባቢዎች አብዛኛውን ስፍራ መቆጣጠር የሚችልበት ሁኔታ ተፈጠረ። ለምሳሌ ቆራሄን፣ፊቅንና የጎዴን አካባቢ ሳይቀር በሰፊው ወደ መቆጣጠር መቃረቡ ተውቆ እንደነበር ዘገባዎቹ ይጠቅሳሉ። በ1992 መጨረሻ አካባቢ አስገራሚ ጥቃት በኢትዮ-ሶማሌ አካባቢ መፈፀም ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ከ1993 እስከ 1996 በአዲስ አበባ በንፁሃን ህዝቦች ላይ ዘግናኝ ሽብሮችን እስካካሄደበት ጊዜ ድረስ ከኢትዮ-ሶማሌ ተጠራርጎ አልወጣም ነበር። በመጨረሻም በመከላከያ ሠራዊት ብርቱ እርምጃ አል-ኢትሃድ የኢትዮ -ሶማሊያ አካባቢዎችን ለቆ እንዲወጣ መደረጉ በጊዜው የተነገረ ጉዳይ መሆኑ የሚታወስ ነው።

ይህ ድርጅት በወቅቱ በመከላከያ ሠራዊታችን ክፉኛ ተመታ። እናም ተሰባስቦ መቀጠል የቀረውን ኃይል ሙሉ ለሙሉ እንደሚያሳጣው አል ኢትሃድ ተገነዘበ። የተረፉት የአል -ኢትሃድ አባላት በአንድነት በአንድ ስፍራ ተሰባስቦ መገኘት ለዳግም ጥቃት እንደሚዳርገውም ታሳቢ ማድረጉን በወቅቱ የወጡ ትንታኔዎች ያስረዱናል። እናም በዚህ እሳቤ አል ኢትሃድ በትናንሽ ቡድኖች ተከፋፍሎ በደቡብ ሶማሊያ ለመበታተን በቃ።

## የአልኢትሃድ ቀለም መቀየርና በሶማሊያ የአሸባሪዎች መግነን

ምንም እንኳን አል - ኢትሃድ እስከ 2002 ባለው ጊዜ በአገራችን እንደ ኦብነግ ያሉ ሀገር በቀል ቅጥያዎችን እያሾለከ የከፋ ጥቃት ቢያደርስም መንግሥት ጥቃቱን በመመከት በድንበር አካባቢ ድርጅቱን የማምከን ስራ መሥራቱን ያስታውሳሉ የወቅቱ ዘገባዎች። ከዚሁ ጎን ለጎን ዳግም ጥቃት ከአል ኢትሃድ እንዳይቃጣ ተፈላጊ እርምጃዎች ከመውሰድ ባለፈ መንግሥት ወደ ጎረቤት ሶማሊያ እንዲሻገር ያስገደደው የሽብርተኝነት ስጋት እንዳላጋጠመው በወቅቱ የተፃፉ ዘገባዎች ያስረዱናል።

ከ2002 በኋላ በሶማሊያ ከአገር በቀሉ አል-ኢትሃድ በተጨማሪ የውጭ ዜግነት ያላቸው የሽብር አካላት መኖራቸውን የሚያሳይ ፍንጭ ታየ። ለአብነት የየመኑ ተወላጅ ሱሌማን አብዱላ በዋነኛነት ይጠቀሳል። ይህ ሰው በኬኒያና በሶማሊያ መካከል

ለመመላለስ ችሎ እንደነበር መረጃዎች ይፋ አደረጉ። ይህ ብቻ ሳይሆን በሶማሊያ ሞቃዲሾ ለረጅም አመታት ተደብቆ መቆየቱ የተደረሰበት ከ2002 በኋላ እንደነበር እነዚሁ ዘገባዎች ያስታውሱናል።

በክፍል አንድ ዘገባዬ የፀረ አሸባሪነት ረቂቅ ህግ መውጣትን ተከትሎ የተፈጠሩ የተዘበራረቁ አስተያየቶችን መነሻ አድርጌ ሽብርተኝነትና የፀረ ሽብርተኝነት እርምጃዎች በኢትዮጵያ የዳራ ምልከታ አቅርቤያለሁ። ለዛሬ ከዛ የቀጠለ እና ለምን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ህጉን ፈሩት በሚለው አተያይ እንደ ዜጋ የሚሰማኝን እንደሚከተለው አቅርቤያለሁ።

## <u>አል ኢትሃድ-አልቃይዳና የሻዕቢያ መንግስት</u>

የፀረ ሽብር ረቂቅ ህጉ መግቢያ ኢትዮጵያ ባላት ጆኦግራፊያዊ አቀማመጥ ምክንያት አሸባሪዎች ለሚሰነዝሩት ጥቃት የተጋለጠች አገር መሆንዋን በማስረዳት ይጀምራል። ኢትዮጵያ ውስጥ የደረሱ ጥቃቶችንም እንደሚከተለው በአጭሩ ያስረዳል።

የዓለም አቀፍ አሸባሪዎች የጥቃት ኢላማና ልዩ ትኩረት ከሆኑት የዓለማችን ክፍሎች አንዱ ምሥራቅ አፍሪካ አካባቢ መሆኑ ይታወቃል።ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አገራችንን በስተምሥራቅ የምታዋስነው ሶማሊያ እ.ኤ.አ. ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ መንግሥት አልባ ሆና የአገሪቷን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ በማይቻልበት ሁኔታ በጦር አበጋዞች ሥር ተከፋፍላ ቆይታለች። በዚህም ምክንያት ዓለም አቀፍ አሸባሪው አልቃይዳና ከዚህ አሸባሪ ድርጅት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው አልኢትሀድ እና የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት መጠለያ ሆና በመቆየቷ ኢትዮጵያ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በአሸባሪዎች በሚሰነዘረው ጥቃትና ጥፋት ምክንያት ለስጋትና ለአደጋ ተጋልጣ ቆይታለች።

ሽብርተኝነት በኢትዮጵያ ህዝብ ሰላምና መረጋጋት ላይ እንደዚሁም አገሪቱ ለዲሞክራሲና ልማት በምታደርገው እንቅስቃሴ ላይ ስጋት ብቻ ሳይሆን አደጋም በማስከተል ላይ ይገኛል። ከዓለም አቀፍ አሸባሪ ተቀፅላዎችና ወኪሎች ጋር በመጣመርም ይሁን በተናጠል እንደ ኦነግና ኦብነግ የመሳሰሉ ፀረ ህዝብ ድርጅቶች የአገራችንን ጂኦፖለቲካል አቀማመጥ ተጠቅመው የኤርትራው የኢሳያስ ቡድን የትርምስ እስትራቴጂ አስፈጻሚ ተላላኪ በመሆን በተለያዩ ጊዜያት የሽብር ተግባር ሙከራ አድርገዋል። በአልኢትሀድ፣ በሶማሊያ አክራሪ የእስልምና ፍርድ ቤቶች፣ በኤርትራው የኢሳያስ ቡድን፣ በኦነግና በኦብነግ በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች የተሞከሩ የሽብር ተግባራት፣ በአገራችን የፀጥታ ኃይሎች፣ በፖሊስ፣ በመከላከያ ሠራዊትና በህዝቡ ጥረትና የተቀናጀ አመራር አማካኝነት እጅግ በርካታዎቹ በጥንስስነታቸው በእንጭጩ ተቀጭተዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ ከመፈፀማቸው በፊት ተኮላሽተዋል። በአጋጣሚ የተፈፀሙ ሽብሮች ቢኖሩም የወንጀሉ ፈፃሚ የሆኑት አሸባሪዎች በፀጥታ ኃይሎች በሳል አሰራርና በህዝብ ጥቆማ ብዙዎቹ በቁጥጥር ሥር ውለዋል።

በመንግስት የጸጥታ ሀይሎችና በህዘቡ ብርቱ ጥረት ብዙዎቹ የሽብር ሙከራዎች እንዲከሽፉ ቢደረግም እስከ ዛሬ በአገራችን በተፈጸሙ ጥቂቶቹ የሽብር ተግባራት ንጹሀን ዜጎች ለሞት በቅተዋል። እንደዚሁም በበርካታ ገንዘብ የሚገመት የግለሰቦች ፣የህዝብና የመንግስት ንብረት ጋይቷል።ለዚህ ዋናው ምክንያት የአሸባሪዎች ጥቃት

ባልታሰበ ጊዜና ቦታ የሚፈጸም በመሆኑ ግቡ ፖለቲካዊ፣ ሀይማኖታዊ ወይም አይዲዮሎጂካዊ ሆኖ የሰላማዊ ሰዎችን ህይወት መቅጨት ላይ ያነጣጠረ ነው።

ከፍ ሲል እንደተገለጸው ኢትዮጵያ የሽብርተኝነት ስጋትና አደጋ በከፍተኛ ደረጃ በአንዣበበት በአፍሪካ ቀንድ የምትገኝ ከመሆኗም በላይ በስተሰሜን በኩል የኤርትራው የኢሳያስ ቡድን የአገራችንን ሰላም፣ ጸጥታና የልማት እንቅስቃሴ ለማናጋት ሆን ብሎ የትርምስ ስትራቴጂ በመንደፍ አንዳንዶቹን አስርጎ በማስገባት እንደዚሁም በአገር ውስጥ ያሉ ጸረ ሰላም ሀይሎችን በማሰልጠን፣ በማስታጠቅና በማሰማራት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሰላማዊ ህዝብና በንብረት ላይ የሽብር ተግባር የመፈጸም ሙከራ ማድረጉ አልቀረም።ይህም በመሆኑ ከጸረ ሰላም አሸባሪ ቡድኖች የሚሰነዘሩ የሽብር ጥቃቶችን በበቂ ሁኔታ በመመከት በላያችን ላይ ያንዣበበውን ስጋት ለመቅረፍ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ተቋማት በህግ ማጠናከሩ እጅግ ወሳኝና ቁልፍ ጉዳይ ነው።ተቋማቱን በህግ ከማጠናከር በተጨማሪ የሽብርተኝነት ጥቃት አስከፊነትና ልዩ ባህሪ ግምት ውስጥ በማስገባት አደጋውን ለመከላከል የሚያስችል ራሱን የቻለ የተለየ ህግ ማውጣት የግድ አስፈላጊ የሆነና መታለፍ የሌለበት ነው።

<u>ህጉ የሽብርተኝነትን አለምአቀፋዊ ገጽታ ያነሳበት አተያይ</u>

ሽብርተኝነት ድንበር የማይገድበው ወይም በአንድ አገር ላይ ብቻ ያነጣጠረና በአንድ የተወሰነ ቦታ ተከልሎ የቀረ ባለመሆኑ አሸባሪዎች ከአንዱ አገር ወደሌላኛው አገር በመዘዋወር ወይም የጥፋት መረብ በመዘርጋት የሚፈጽሙት በመሰሪነት ላይ የተመሰረተ እኩይ ተግባር ነው። በዚህም የተነሳ ችግሩ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው ነው። በመሆኑም ሽብርተኝነትን ለመዋጋት አገራት፣ መንግስታትና ህዝቦች በትብብርና በጋራ መስራት የግድ ይጠበቅባቸዋል።ይህ ሁኔታ በዓለማችን ውስጥ በበርካታ አገራት ግንዛቤ በማግኘቱ በተባበሩት መንግስታት ድርጅትም ሆነ በተለያዩ አህጉራዊና አካባቢያዊ ድርጅቶች በዓለም አቀፍ ግንኙነት ደረጃ ቦታ የተሰጠውና የተረጋገጠ ነው።ይሄም በመሆኑ ሽብርተኝነትን ለመከላከል የሚያስችሉ 12 የዓለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ በመመርኮዝ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት በቁጥር 1373(2001) ውሳኔ አሳልፏል። ሽብርተኝነት በዓለማችን ሰላምና ደህንነት ላይ የተጋረጠ ስጋትና አደጋ እንዲሁም የተባበሩት መንግስታት የተቋቋመባቸውን ዓላማዎችና መርሆዎች የሚጻረር ለመሆኑ የሰላም ጸርነቱን አስመልክቶ በዓለም አቀፍ የጸረ- ሽብር ውሳኔዎች ላይ የሰፈሩት ነጥቦች ያረጋግጣሉ።

<u>የሽብርተኝነት ስስ ግቦችና የረቂቅ ህጉ አተያይ</u>

ሽብርተኝነት የተወሰኑ ቡድኖች ወይም ክፍሎች የፖለቲካ ዓላማቸውን ወይም አመለካከታቸውን በማስፈራራትና ሀይልን በመጠቀም በህዝብ ላይ ለመጫን የሚፈጽሙት ወይም የሚሞክሩት አደገኛና አሰቃቂ የጥፋት ተግባር ነው ።

እስከ ዛሬ ከተግባር እንደታየው ሽብርተኝነት በህዝብና በመንግስት ላይ ስጋት የሚያስከትል ተግባር እንደሆነ ቢታመንም በአብዛኛው የጥቃት ኢላማ አድርጎ የሚንቀሳቀሰው በሰላማዊ ህዝብ ላይ ነው።ይሄም በመሆኑ አሸባሪዎች የንጹሀን ሰዎችን ህይወት በማጥፋትና የህዝብ መገልገያ ተቋማትን በማውደም ላይ ያተኮረ እጅግ አስከፊ የሆነ ኢ- ሰብአዊ ድርጊት ሲፈጽሙ ተስተውሏል።

ሽብርተኝነት ህዝቦች በሰላም፣ በነጻነት፣በተረጋጋ ሁኔታ ኑሮአቸውን እንዳይመሩ አደገኛ እንቅፋት በመሆኑ የሰው ልጅ የሆነ በሙሉ እጅግ የሚሰጋውና የአእምሮ እረፍት የሚነሳው በመሆኑ ለህዝቦች ሁሉ ሽብርተኝነትን መዋጋት የህልውና ጥያቄና ግዴታ ሆኗል።

ከእለት ዕለት እየረቀቀ የመጣው ሽብርተኝነት፣ የወቅቱ የአለማችን አሳሳቢና ከፍተኛ ስጋት እየሆነ በመምጣቱ በርካታ ሀገራት ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት በመስጠት ላይ ናቸው። በዚህም ምክንያት የተለያዩ አገራት የሽብርተኝነትን አስከፊነት፣ አደጋና የአፈጻጸሙን ውስብስብነት ግምት ውስጥ በማስገባት ራሱን የቻለ የወንጀለኛ መቅጫ ህግና ወንጀሉን የማጣራት ሒደት ስርዓት አውጥተው እየሰሩበት ይገኛሉ።ከነዚህ ውስጥ እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ ካናዳ፣ አውስትራሊያ፣ህንድ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ዩጋንዳ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

## ለሽብርተኝነት ለምን የተለየ ህግ አስፈለገ?

በሽብርተኞች የሚሰነዘሩ ጥቃቶችም ሆኑ የጥቃት ሙከራዎች እንደሌሎች የተለመዱ ደረቅ ወንጀሎች ወይም ግለሰባዊ ጥቃቶች የሚታዩ አይደሉም። አሸባሪዎች ጥቃት የሚፈጽሙት የራሳቸውን የፖለቲካ ዓላማ ወይም አመለካከት በሀይልና በማስፈራራት በሌላው ህብረተሰብ ላይ በተጽእኖ ለማሳረፍ ሲሆን የሽብር ወንጀሉን ከጥንስሱ እስከ ፍጻሜው ድረስ በረቀቀና ውስብስብ በሆነ መንገድ እንዲሰራ በማድረግ የጥፋት ኢላማውን በተገኘው ህዝብና ቁስአካል ላይ በማነጣጠር የሚፈፀም ነው። በመሆኑም ድርጊቱ እጅግ የከፋና የተለየ በመሆኑ ጥቃቱን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በቂ የሆነና የተለየ ህግ ሊቀረፅለት ይገባል። ለዚህም ዋነኛ ምክንያት የሽብር ተግባር የሚጠነሰሰው፣ የሚፈጸመውና በኋላም የሚያስከትለው ጉዳት ከሌሎች የተለመዱ ወንጀሎች በሁለንተናዊ ባህሪውና ይዘቱ የተለየ በመሆኑ ነው። ይህም ሲባል

ሀ/ ሽብርተኝነት ፡- ንፁህን ሰዎችን ማጥፋት ላይ ያተኮረና በጅምላ የተገኘውን ህብረተሰብ የጥቃቱ ሰለባ የሚያደርግ ሆን ተብሎ፣ ታስቦና ታቅዶ የሚፈጸም፤ የተወሰኑ ግለሰቦችን ሳይሆን የአጠቃላይ የህዝቡና የአገር ቀንደኛ ጠላት ከመሆኑ በተጨማሪ የሰላማዊውን ህዝብ ኑሮ ለማናጋት ዘወትር የስጋት ምንጭ ሆኖ የህብረተሰቡን ህሊና በማወክ የሚያስከትለው ጉዳት እጅግ የጎላ በመሆኑ

ለ/ ሽብርተኝነት፡- የአገራችንን ኢኮኖሚ በማሳደግ ህዝቡን ወደተሻለ ኑሮ ለማምራት የምናደርገውን ጥረት የሚያደናቅፍና በግል፣ በህዝብና በመንግስት የተሰሩ የልማት ተቋማትን በማውደም የጥፋት ተግባር ላይ ያነጣጠረ አደገኛ ጸረ ልማት እንቅስቃሴ በመሆኑ ነው።

## 'ከፍርሃታችን ፍሩ' ከተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አተያይ በስተጀርባ

የፀረ ሽብርተኝነት ህጉና የአገራችን የሽብርተኞች ጥቃት ዳራ ይህ ሆኖ እያለ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለምን ይህን ህግ ፈሩት? ለምንስ ፍርሃታችንን ካልፈራቹህ ይሉናል? የሚለው ጥያቄ ሌላው መመለስ ያለበት ጉዳይ ነው። ከሰሞኑ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ ሁለት ገፅታዎች በቅድሚያ እንመልከት።

በዋናነት ቀደም ብለን የገለፅናቸው አለም አቀፍ አሸባሪዎች የአገር ውስጥ ተላላኪ ፈጥረው በፈፀሟቸው የሽብር ድርጊቶች ውስጥ አነሰም በዛም በህጋዊና ሰላማዊ ትግሉ አለን የሚሉ ድርጅቶች ውስጥ ያሉ አባላትና አንዳንድ አመራሮቻቸው መገኘታቸው ነው።

ለዚህ በቂ የሆነ መረጃ እንዲሆነን ህዳር 14 ቀን 2001 በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ የወጣውን ዜና መለስ ብለን እንመልከተው። ሕጋዊ የፖለቲካ ድርጅቶች አሸባሪዎችን የመዋጋት ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነት አለባቸው በሚል ርእስ የብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎትና የፌዴራል ፖሊስ የጋራ ፀረ-ሽብር ግብረ ኃይል ያወጣው መግለጫ ከስረ መሰረቱ ነገሩን በደንብ ያስረዳናል።

የብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎትና የፌዴራል ፖሊስ የጋራ ፀረ-ሽብር ግብረኃይል የኦብኮና የኦፌዴን ድርጅቶች አባላት የሆኑ ግለሰቦች በተለያዩ ጊዜያትና በተደጋጋሚ በሽብር ተግባር ሲሳተፉ መያዛቸውን ይገልፃል።እናም የአሸባሪውን የኦነግ ዓላማ አንግበው የሽብር ተግባር በመፈፀም፣ ለተመሳሳይ ዓላማ ቅስቀሳ በማድረግ፣ ሰዎችን በማደራጀት ተግባር ላይ ተሠማርተው በመገኘታቸው ለሕግ እንዲቀርቡ መደረጉንና ድርጅቶቹ እንዲህ አይነት አባላት ላይ አቋም እንዲወስዱ ጠይቆ ነበር።

በተጨማሪም የዚሁ የሽብር ተግባር አራማጅ የነበሩና ከሕግ አምልጠው ወደ ኤርትራ በመሔድ የሻዕቢያን የትርምስ ስትራተጂ በተላላኪነት ከሚያስፈጽመው ኦነግ ጐን በይፋ የተቀላቀሉ እንደሚገኙም ይፋ አደረገ።ከነዚህም መካከል በፓርላማ መቀመጫ የነበራቸውና ከሕግ ተጠያቂነት በመሸሽ ወደ ኤርትራ ሄደው ኦነግን በይፋ ከተቀላቀሉት መካከል የኦብኮ አባላት የነበሩት ተሾመ በዳሳ ጨልቹሶ፣ አባቡ አብዶ ፍሪ፣ ሲራጅ ሁሴን ሰዎ፣ ኢካሳ ከሲ ጋሪ እና ግርማ ጫላ እንደሚገኙበት በማስረጃነት ጠቅሷል።እንዲሁም የኦፌዴን አባላት የነበሩት ዶክተር ጌታቸው ጅጊ፣ የአብዮት ከበደ፣ ሣራ ማሞ እና ጌታቸው አመንቲ የተባሉት እንደሚገኙበትም በማከል።

በኦነግ የሽብር ተግባር ተሳታፊ በመሆን ለሕግ ቀርበው ከተፈረደባቸው የኦፌዴን አባላት መካከልም ጉደታ ሹቤ፣ አሸናፊ አዱኛ እና ኢትዮጵያ ተመስገን አያንሳ የተባሉትን እንደ አብነት መጥቀስ እንደሚቻልም ነበር የተዘገበው።መግለጫው በእነዚህ አሸባሪ አባሎቻቸው ምክንያት ድርጅቶቹን በሕግ መጠየቅ እየተቻለ፣ በውስጣቸው ስላሉት የአሸባሪው ኦነግ ዓላማ አራማጆች እንቅስቃሴ በበቂ ሁኔታ አያውቁም፤ ድርጊቱንም አይደግፉትም ከሚል ቀና አመለካከት ድርጅቶቹን በሕግ ወደመጠየቅ አለመኬዱን በመግለፅ የመንግስትን የታጋሽነት ወሰንም አስረዳ።

ይሁንና ኦህኮና ኦፌዴን በጉያቸው የተሸሸጉትን አሸባሪዎች አጋልጠው ለሕግ የማቅረብ ኃላፊነታቸውን መወጣት ሲገባቸው ይባስ ብለው በዚህ የሽብር ተግባር የተያዙ አባሎቻቸውን ለሕግ ለማቅረብ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለማደናቀፍና የፍርድ ሂደቱ ላይ ሕገ ወጥ ተፅዕኖ ለማሳደር ሙከራ ሲያደርጉ መስተዋሉ ደግሞ ሌላው በሰላማዊ ትግል ውስጥ ካለ ድርጅት የማይጠበቅ ነበር።

እናም ኦብኮም ሆነ ኦፌዴን በሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት ሕገ መንግሥቱን ተቀብለናል፣ እናከብራለን በሚል ለሕዝቡ ቃል ገብተው መሆኑን

አመልክቷል። የገቡትንም ቃል የማክበር ኃላፊነት እንዳለባቸውም መንግስት አሳሰበ። በዚህም መሠረት ድርጅቶቹ በውስጣቸው ተሸሽገው ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሽብር ተግባር ለመናድ የሚንቀሳቀሱትን አንቅረው ሊተፉዋቸው እንደሚገባም መንግስት በተጨማሪ አሳስቦ ነበር።

የነዚህ ድርጅቶች ፍርሃት እንግዲህ ይህ ከሆነ ብዙም ላያስጨንቀን ይችላል፤ ምርምርም አያስፈልገውም። ነገር ግን ድርጊታቸው ከሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ትግል የመውጣት ትክክለኛ አዝማሚያቸው ሆኖ ሳለ በህገ መንግስቱና በአለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች ካባ ተሸፍነው የፀረ አሸባሪነት ህጉን ይቃወማሉ። እናም ፍርሃታቸው አያስፈራንም። ለምን ቢሉ እውነተኛ ፍርሃታቸው አንድ እግራችን በሰላማዊ ትግል ሌላው እግራችን በአሸባሪ ድርጅቶች ሆኖ የተገኘ እለት ምን ይውጠን ይሆን የሚል ስለሆነ። በዚህ ወቅት የሚያዋጣው ግን መንግስት እንደገለፀው አንድ እግሩ የአሸባሪዎች መረብ ውስጥ ያለ የድርጅቱ አካል ከወዲሁ ሰብሰብ ብሎ ወደ ሰላማዊ ትግል ወረዳ የሚገባበትን መንገድ መቀየስ ብቻ ነው። ፍቱን መድሃኒት ተደርጎም የሚወሰደው ይሄው ነው።

እናም እግርን ሰብሰብ አድርጎ በዴሞክራሲ የጫወታ ሜዳ ለመግባት ቁርጠኝነት ማሳየት ለሁለት ነገሮች ይጠቅማል። አንዱ እነዚህ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሰላማዊ ትግል ጎራ እስካሉ ድረስ በዴሞክራሲ ጨዋታ ህግ ውስጥ እንደፈለጉ እንዲጠቀሙ የፀረ አሸባሪነት ህጉ የሰላምና ደህንነት ጥላ ከለላ ይሆንላቸዋል። ሌላው የፖለቲካ ድርጅቶቹን ቁርጠኛ አቋም ህዝብና መንግስት አውቆት እንዲያከብራቸውና እምነት እንዲጥልባቸው ያስችላል። አለበለዚያ "ተሁለት ዛፍ የወደቀ"ን ያመጣል።

**---END---**